የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፸፫
አዲስ አበባ ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year, No.73
ADDIS ABABA, 16th May, 2016

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፵፱ /፪ሺ፰ ዓ.ም

በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮርያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ............ገፅ ፱ሺ፷፪

አዋጅ ቁጥር ፱፻፵፱/፪ሺ፰

**በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮርያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮርያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት ህዳር ፳፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ ፮ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**CONTENTS**

Proclamation No.949 /2016

Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the People's Republic of Korea for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation........................................................page 9062

**PROCLAMATION No. 949/2016**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE CONVENTION BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE PEOPLE'S REPUBLIC OF KOREA FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION AND THE PREVENTION OF FISCAL EVASION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME**

**WHEREAS**, a Convention for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income has been signed between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the People's Republic of Korea on the 5th day of December 2012, in Addis Ababa;

**WHEREAS,** the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said convention at its session held on 14th day of April , 2016;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮርያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፵፱/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **<u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮርያ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ህዳር ፳፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችለው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. **<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

፬. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the People’s Republic of Korea for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No.949 /2016”.

2. **<u>Ratification of the Convention</u>**

The Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the People’s Republic of Korea for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income signed on the 5th day of December 2012 is hereby ratified.

3. **<u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to implement the Convention in cooperation with the concerned government organs.

4. **<u>Effective Date</u>**

This proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 16th day of May 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት